<u>**የምርጫ ሆያሆዬ፣ ጉራማይሌ ፖለቲካና ስህተትን ደገማ**</u>

**ሀማ ቱማ**

**ቃላት ትርጉም አላቸው:: የቃላትን ትርጉም በዘፈቀደ የሚያጎብጡ ወይም ሊቀያይሩ የሚፈልጉ አምባገነኖች በየጊዜው ብቅ ማለታቸውም የሚታወቅ ቢሆንም የጥቁር ትርጉሙ ነጭ ሊሆን አይ ችልም:: ምርጫ ሲባልም የታወቀ ትርጉም አለው:: ደርግና ወያኔ ግን በዚህ ቃል/ፅንሰ ሀሳብ ላይ ሲያላግጡ ቆይተዋል:: ቃላትን ትርጉም አልባ የሚያደርጉ ብዙ ናቸው:: የአፍሪካ ሀገሮች ዛሬ የ 50 ዓመት ነፃነትን አከበሩ ሲባልም ነፃነት ተብዬው ቀፎና ባዶ መሆኑን፣ ትርጉም አልባ መደረ ጉን የምንስተው አይደለም:: መፈክሮችም ከተጨባጭ ትግልና ይዘት ውጪ ቢጮኹ ቃሎቹ ፍሬ ቢስና መልዕክት-አልባ መሆናቸው ሊደበቅ የሚችል አይደለም::**

**የምርጫ ሆያ ሆዬ መባሉ የሂደቱን የሕፃን ጨዋታነት ከመጠቆሙ ሌላ ጊዜው ወያኔ የሚሉት ዘረኛና ችጋርን ቀፍቃፊ ጉድ የሰፈነበት ነውናም ሆያ ሆዬው የሚያስገኘው ሙልሙልም አለመ ኖሩን ጠቋሚ ነው:: በ1997 ዓ.ም. የነበረው ሁኔታ ዛሬ ካለመኖሩ ሌላ ያኔ ሕዝብ ደሙን አፍሶ ሊይዘው የጣረው መሰረታዊና ዘላቂ ለውጥ  የሚያዝና የሚጨበጥ ሳይሆን ቆይቷል:: አላሚው ባይጠፋም ህልሙ ለብዙዎች እልም ያለ ይመስላል:: ያኔ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተባበሩ ተቃዋ ሚ ሀይሎች ዛሬ ስንጥቅጥቃቸው ወጥቶ ያሉ መሆናቸውን መታዘባችን የሚካድ አይደለም:: ገዢ ው ቡደንም የተዳከመ መሆኑ ግልፅ ነው-- ምንም እንኳን ተፃራሪዎቹ ካላቸው ድክመት አንፃር የጠነከረ መሰሎ ቢታይም:: የራሱ የቀድሞ ብፃዮች ቢያንስ ግብዙን ቁንጮአቸውን ሊያስወግዱ አምርረዋልና በዚሁ ደረጃ አስቸጋሪ መሆናቸው ይታያል:: መለስ ድንጉጥ ፍጥረት እንደመሆኑ መጠን ቢደናበርም ያለፈውን ስህተት አንደግምም ባለው መሰረት ምርጫውን ለማጭበርበር ዝግጅቱን ጨርሷል:: ተቃዋሚ ሀይሎች ግን ያለፈውን ስህተት ለመድገም ዓይናቸውን ጨፍነው ሊገቡ የወሰኑ መስለዋል:: ግንቦት ሩቅ አይደለምና ይህን ጎጂ ምርጫ የምናየው ይሆናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ዛሬም እንደትላንት አስገራሚ ክስተቶችን ሊያሳየን መቻሉ መጠበቅ ያለበት ነው:: የካቲት 66 ንም ሆነ ግንቦት 1997ን የጠበቁ ብዙዎች አልነበሩም::**

**የፖለቲካውን መድረክ ያጣበቡት የታሪክ ላፒሶች፣ወንጀል ሸፋፋኞች፣የቋንቋም ሆነ የፖለቲካ ጉራማይሌ ጠበብቶች በመሆናቸው የነፃነት ፍለጋው ጉዞ የጨለማ መደናበር ሆኖ አስቸግሮናል:: ፊቅ አልን ስንል የጓልዮሽ መንሸራተቱ የቤት ልጅ ሆኖ ተወዝፎብናል:: በ 1997 የተሞከረው በደም ታጥቦ ልንረሳው የማይገባ ተመክሮን ለግሶናል:: ይህን አልገነዘብ አልማር ማለቱ ደግሞ ስህተት ብቻ ሳይሆን ሀጢያትም ወንጀልም ሊባል የሚገባው ነው:: ወያኔ በሰላም ስልጣን ሊለቅ በፍፁም የሚታሰብ ጉዳይ አለመሆኑን ገልጦልናል:: የትግል መሪዎች ነን ብለው  ባሩድ ሊጤስ ሲዳዳው (ያውም ተተኩሶ ሳይሸት) ሽብረክ የሚሉ፣ ለባለነፍጥ የሚሰግዱና ሕዝብን የሚከዱ ማፊሪያዎች መኖራቸውንም አሳይቶናል:: ታሪክን መርሳት ምንኛ ጎጂ ሊሆን መቻሉንም የወገኖ ቻችን ደም ሲፈስ በፃፈው መልዕክት መረዳት ተገደናል::  ከዚያም በላይ የዘረኝነትን ቁሻሻነትን**

ም ፀረ ወያኔ ነን ብለው ከርመው የወያኔ ወድቀት ሲያንዣብብ ዘር ከልጓመ ይስባል ሆኖባቸው፤ ከወያኔም ወያኔ ሆነው ሲያጓሩ በማየት መረሳት የሌለበተ ትምህርትን ሰጥቶናል:: ያኔ የተሰዉት ወገኖች ደም ዛሬም ይጮሃል:: ያኔ ለእስር የተዳረጉት ወገኖች ዛሬም በዚያው ይሰቃያሉ፤ተፈታ የነበረችውም ብርቱካን ሚዲቅሳ ታፍና ተደባልቃቸው በቃሊቲ ፍዳዋን ትቀበላለች:: ከዚህ ሁሉ የተገበየ ትምህርት መኖሩ ግን በጣም አጠራጣሪና አነጋጋሪ ነው:: መሪያቸው ታስራ ትፈታ ብለ ው ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ ሲገባቸው ባትፈታም ለምርጫ ዝግጁ ነን ከማለት አልፈው እርስ በርስ ሲከፋፈሉና ሲደባደቡም ማየቱ የወያኔ ፌሽታ ሆኖ ሕዝብን ግን አሳዝኗል:: የወያኔ ተቃዋሚ ነን እያሉ ግና በግልባጩ የደርግንም ሽብር እየካዱና ከዘረኝነቱ ማጥ መውጣቱ ያቃታቸው ወይም ለወንጀላቸው ይቅርታ ሕዝብን መጠየቁ የከበዳቸው፤ ነፃ ሊያወጡ ቀርቶ ህሊናቸውን በፀፀትና በንስህ ነፃ ማውጣት ከቶም የከበዳቸውን አንዳንድ ዜጎች መሪ ብለው ሊያቅፉም ዳግም ሊሳሳቱም ሲነሱ ማየት ተገደናል:: በምርጫ አለመሳተፍ ለወያኔ ድልን ማስረከብ ነው የሚል ክርክር ይደመ ጣል:: ነፃ አለመሆኑ በታወቀ ምርጫ ተሳትፎ ለአረመኔ አገዛዝ ሽፋን ሰጪና አዳማቂ መሆን ጥፋ ት መሆኑን ግን ተመክሮአችንም ሆነ የበርማ፤ የሱዳን ወዘተ ተመክሮ ሁሉ ያሳየን ሀቅ ነው:: ማዕቀብ ማድረጉና በወያኔ ምርጫ አንሳተፍም ማለቱና በሚያዋጣ ትግል መሰማራቱ በተገባ ነበር :: ዳግም እንሞክር በሚለው መንጎዱ ከተፈለገም መነሻው የወያኔን አገዛዝ ፀረ ሕዝብነትና ፀረ ኢትዮጵያነት ተቀብሎ መደረጉ የተሻለ በሆነ ነበር:: ሂደቱን ወያኔን ይበልጥ ለማጋለጥና ለመጉዳ ት ለመጠቀም ማለት ነው:: መለስ ዜናዊ ወዮላችሁ ማዕቀብ ታደርጉና በሚል ሊያጓራ የሞከረው የሚቆነጥጠው ሂደት ወይም ክስተት መሆኑን ጠቋሚ ነው:: እምቢኝ ለማለት ዛሬም ጊዜ አለ::

ይህ ሳይሆን ቀርቶ የወያኔን አገዛዝ ጠላትነት ተክዶ፤ የወያኔ አገዛዝ መደምሰስ አለበት የሚለው መፈክር ያልሰለጠነ ተብሎ፤ ዛሬም ጊዜ ያለፈበትን የዕርቅና ሰላም መፈክር ለማስተጋባት መነሳ ቱና በወያኔ ምርጫም ለመሳተፍ መንሰፍሰፉ ስህተትን ደገማ ቢባል የሚያንሰው ነው:: ፖለቲካ ማንም ገብቶበት የሚንቦጫረቅበት ወንዝ የመሰላቸው ስለበዙ ብቻ ይሁንላችሁ ቧርቁበት ተብሎ ሊተውላቸው አይገባም:: ግብግቡ የመሸታ ቤት የሰካራሞች ሞክረኝ ላሳይህ አይደለም:: የሀገርና የሕዝብ ህይወትና የነገ ዕጣ የሚዳኝበትና የሚወሰንበት ነውና የሞት ሽረት ጉዳይ ነው:: በባዕድ ሀገር የተኩራሩ ምሁራን በሉን ባዮችም የሚወስኑበት ጉዳይ አይደለም:: የሀገር ዕጣና ዕድል ወሳኝ ምርጦች ነን ባይ የሚንቁት ሕዝብ የሚወስነው ነው:: ይህን የሚክዱ ወይም መቀበል ያቃታቸው አምባገነኖች ሆኑ ዕብሪተኛ ምርጥ ነን ባዮች ሁሉ ውሎ አድሮ በሕዝብ ፊት ለታሪካ ዊ ፍርድ የሚቀርቡ መሆናቸውን ታሪክ ራሱ ያረጋግጥልናል:: ውሎ አድሮ ታጥቦ ጭቃነት ንቃትና ስልጣኔ ሳይሆን ውርደት ነው :: የሀገራችን ሕዝብ መከራ በመከራ እየተባዛበት፤ ጭንቀ ትና ስቃይ ተደማምረውበት ራሱን ቢደፋ በላቡ ያስተማራቸውና የባዕድ ሎሌ ሆነው ሊዘባነኑበት የተነሱ ከበርን አወቅን ባዮች እየናቁት ላንተ ሚበጀውን ወሳኝና አስፈፃሚ እኛ ምሁራን ነን ብለ ው ሲጮሁበት፤ ትላንት ጦርነት ሊሰሩበት የዛቱትም ዛሬ አለእኛ በጎ ፍቃድና አመራር ነፃ አትወ ጣም ብለው ሲያሾፉበት፤ በ 1997 የካዱትም በ2002 ያንኑ የገለማውን መርሀ ግብርና አቅዋም

ይዘው አለንልህ እያሉት፣ ከትላንት ወዲያ የሸብር አራማጅ ፓርቲ ቀንደኛ አባል ሆነው በደሙ ና መስዋዕትነቱ የቀለዱ ዛሬ መሪህ ነን ሽብርም አልተፈፀምብህም ብለው በይፋ ክደው ሲያላግ ጡበት፣ ገዳዮቹ ታዳጊው ሊመስሉ ሲቃጡ በተወነባበደ ሁኔታ የጉራማይሌ ፖለቲካ አራማጆችን ሻጥርና ሴራ ሊያስወግድ መቻሉ ተፈታታኝ ግዳጅ ሆኖበታል:: ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ ብቻ ሳይሆን የበግ ለምድ ለባሾች ቀበሮ መሆናቸውን ማወቁን በዋጋ ክፍያ (በደምም ክፍያ) ማወቅ እየተገደደ ነው:: መድረኩ ውጥንቅጡ ስለወጣም ደጋፊ ነን ያሉት የትላንት ጀግናቸውን ወይ ድርጅት ሲያብጠለጥሉና ሌለውን ሲያቅፉ፣ ለምሳሌ ፕሮፌሰር መስፍን በወያኔነት ስዬ አብረሀ ደግሞ በፀረ ወያኔነት ሲፈረጁና ሲዘለፉ ወይም ሲሞገሱ ለመታዘብም በቅተናል:: ቢዘባረ ቅም ግን ወሳኝ ጊዜ ላይ መድረሳችን ይታያል:: ገዢው ቡድን ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ቢዘጋጅ ም ሊያመልጠኝ ይችላል ስጋቱ ልብ ደካም ሊሰጠው ሲሞክር እየታየ ነው:: የተማመነበት ክፍል ሊከዳው የቆመበት መሰረትም ሊናድ መቻሉን መገንዘብ ተገዶ ይህን ፍርሀቱንም በመለስ ዜናዊ የድንጉጥ ድንፋታ እያጋለጠ ነው:: የበላይነቱን ይዞ ፍርፋሪ ወይም ሰባራ ወንበሮችን ለአጃቢዎቹ በመለገስ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ለማስመሰልና ምርጫውንም ማጭበርበሩን ለመደበቅ መጣሩ የሚ ጠበቅ ነው:: ጡት አባቶቹም ከአፋዊና አስመሳይ ቁጣ ባሻገር ምንም የረባ ተፅዕኖ እንደማያደርጉ በት ወያኔም በልቡ ያውቃል::

የሀገራችን አንገብጋቢ ጥያቄዎችና የሕዝብ ብሶቶች ገንባር ቀደምነትን ይዘው የትግል ዋና መፈ ክር ሆነው በሚገባ አለመቅረባቸወም ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም:: የሀገራችን መሬት ተቆርሶ ለባዕድ መሰጠቱ፣ የሀገራችን ለም መሬት ለባዕዳን መሸጡ፣ ሰርቶ አደሩ ሕዝብ ለአሰከፊ ብዝበዛ ና ደህነት መጋለጡ፣ የሀገር ንብረት ወርቅ ምርት ሁሉ በጥቂት ወያኔዎች መዘረፉ፣ ዘረኝነት መጠናከሩና ሕዝብ መበደሉ፣ ንፁሃን መገደላቸወና መታሰራቸው አነጋጋሪና አከራካሪ ሆነው ጆሮ ና ህሊናን አልደበደቡም:: የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ የኑሮ ውድነት ይወገድ፣ የሀገር ሉዐላዊነት ይከበር፣ ፍትህ አይጓደል የሚል አንድም ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ ሲካሄድ ለማየት ዓይናችን አልታደለም:: ይባስ ብለው የድርጅት መሪዎች ነን የሚሉት ከዱርቤቴና አርባ ምን ጭ ይልቅ ሎስ አንጀለስና ዋሺንግተንን መጎብኘቱና በባዕድ ሀገር ያለውን መቀስቀሱንም መርጠ ው ላይ ታች ሲሉ መታዘብ ዕጣችን ሆኗል:: ለሰብዓዊ መብት መከበር አንዴም ሲሰለፉ ያልታዩ ትም በድርጅታቸው ላይ ሲሰለፉና በርስ በርስ ግጭትም በለው ሲባባሉ ጉድ አይሰማ ጆሮ አሰኝ ቶናል:: ዝብርቅርቅ ያለ ፖለቲካ ሰፍኖ ሊያፍነን በመቃጣቱም ባለህበት እርገጡ ምፀት አልተን እንዳለ ነው:: በሀገራችን ጉዳይ በአዛኝ ቅቤ አንጓች ዓይነተ ጣልቃ የሚገቡትም መፍትሄ ሳይሆን ችግርን እያባባሱ ቀጥለዋል:: በአስመራ ከተማም ያወም በሻዕቢያ ድጋፍ አዲስ የአማራ ድርጅት በ1997 የአግአዚ ጦር አዛዥ በነበረ ሰው ተመስርቻለሁ ብሎናል:: በሱዳን የተጭበረበረው ምር ጫና ሀገሪቷን ሊከፍል የሚችለው መጪው ሕዝብ ውሳኔ፣ በሶማሊያ የአክራሪዎች መጠናከር፣ ከኤርትራ ጋር ያለው ሁኔታ መቃቃር መቀጠሉ፣ግብፅ ኢትዮጵያን ለማዳከም አግኝታ የማታው ቀውን ዕድል በወያኔ መለገሏ-- ይህ ሁሉ ነገን አሳሳቢ ማድረጉ አልቀረም:: ሀገርን ማዳን ተልዕ ኮም በዚሁ ይበልጥ እየከበደ መሄዱ መታየትም ያለበት ይሆናል:: ከዚህ አንፃርም የምርጫው

ሆያ ሆዬ ዋና ተልዕኮና ችግርን ጋራጅና ሽፋኝ ጢስ ከመሆን ሌላ ምንም ፋይዳ የለውም ብንል ስህተት አይሆንም:: ወያኔ ከምርጫው ባሻገርም ሊቃወሙት በሞከሩት ላይ የአፈና አርምጃውን ለመውሰድ መዘጋጀቱም የሚታይ ነው:: 2002 የዴሞክራሲ ሳይሆን የአፈና ዓመትና በዚሁም ረገድ የ1997 መንታ ሆኖ ቀጣይ ነው::

ደግመን ደጋግመን የሕዝብ ጎራ ችግሮችን በማንሳት የፅዳት ዘመቻን መጠየቃችን ገበናን በአደባ ባይ ለማስጣት ሳይሆን  ድክመቶቹ ካልተወገዱ ትግሉ ሊሰምር ባለመቻሉ ነው:: ምስጢር መጠበ ቅ አለመቻል ከነዚህ ችግሮችና ድክመቶች አንዱ ሲሆን ወያኔ በሰርጎቦቹና ሰላዮቹ አማካይነት ድርጅቶችን በሚገባ ሊያውቃቸውና ሊበጠብጣቸው--ሊያጠቃቸው መቻሉም እየደረሰ ባለው ጉዳት የሚታወቅ ነው:: ድርጅቶች ሕዝብን ሊመሩ ካለመቻላቸው ሌላ ሕዝብንም ሊተኩ መነሳ ታቸው ቀጣይ ስህተታቸው ሆኖ ይገኛል:: ከመታገል በፊት ካባ መልበሱ እየቀደመ፤ ተክለሰውነ ት የጋራ ጥረትን እያዳከመ፤ ብቃት አልባዎች በወሳኝ ቦታ እየተገኙ ሲያደፈርሱ፤ ዜጎችም በቻል ተኝነት መብታቸውን ለነዚሁ አሳልፈው እየሰጡ ወይም እያስነጠቁ፤ የወያኔን ዕብሪት የሚያስቆ ሙ እርምጃዎች አልታይ ብለው፤ ሊወድቅ ያለውን አገዛዝ ገፍቶ የመጣሉ ቁርጥ ምትም ዘግይቷ ል:: ሕዝብም ሀገሩን ለማዳን በሚገባ መደረጃት፤ ተደራጅቶ ለመታገልም መድፈር እንዳለበት ደግሞ ደጋግሞ መጮህ የማይታለፍ ሆኖብናል:: በጎበዝ አለቃ በየቦታው ተነስ ጥሪ የተስተጋባው ም ለዚሁ ነው:: በነጠላና በቡድን በሁሉም መስክ በወያኔ ላይ ጥቃት ማድረስ፤ ክብሪትም ትጥቅ ነ ው፤ ማዕቀብም ተገቢ ትግል ነው ብሎ በወያኔ ላይ ጥቃትን በተካተታይ ማደርሰና ፀረ ሕዝቦችን ማሸበር ወቅታዊ ነው:: ለሕዝበና ለሀገር ብሎ ህይወቱን ሊሰዋ የሚመጣ ባዕድ የለም፤ ይመጣል ብሎ መጠበቅ ራሰን ማጃጃልና የጭቆና ቀንበርን በራስ ላይ ይበልጥ ማጥበቅ ነው:: በመሆኑም በወያኔ የምርጫ ሆያ ሆዬ አማካይነት ወይም መንገድ ለውጥን መጠበቁ ከንቱ ነው ማለት የግድ ይሆናል:: የሚጠበቀዉም ለውጥ መንግስቱን በመለስ የተካው ዓይነት ጉልቻ ቅየራ እንዳይሆን ከወዲሁ ነቅቶ መታገልን፤መጣርን ይጠይቃል::

ስህተትን መድገም ሀገርን ያስነጥቃልና፤ የመለስ መንጋ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ ቆርጦ የተነሳ ከይሲ ቡድን ነውና  የመሳሳት ቅንጦት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልተሰጠውም ብንል ትክክል ነው:: ወያኔ በሰላም ስልጣን ይለቃል ብሎ መሳሳት፤ በምርጫ ይሸነፋል ወይም የሕዝብን ድምፅን አክብሮ ይገኛል ብሎ መሳሳት፤ ከዘረኝነቱ ተላቆ ኢትዮጵያዊ ስሜት ይሰርፅበታል ብሎ መሳሳት፤ ርህራሄ ን ይላበሳል ህቅንም ይናገራል ብሎ መሳሳት ዛሬ በ 2002 ዓመተ ምህረት፤ ወያኔ ለ 19 ዓመት ሀገ ረን ሲያደማ ካየን በኋላ በዚህ መንገድ መሳሳት ሀገርን የሚያሳጣ ጅልነት ነው:: ሕዝብ ደግሞ አዋቂና ብልህ እንጂ ጅል ሆኖ፤ ሀገሩንም ለባዕድ አሳልፎ መስጠት የለመደ ሆኖ አይታወቀም:: አዲስ የምናፍርበት ታሪክ እንዳይፃፍ  መከላከል ግዴታችን ነው:: እስካሁን በተካሄደው ትግል የወያኔ አገዛዝ መደላደል ህልም ሆኖበት እንዲገኝ መደረጉ የሚታወቅ ነው:: ህብረተሰባዊ መሰረ ቱ ጠቧል፤ በአውራጃዊ ስሜት እየታመሰ ነው፤ አምባገነኑ በሎሌዎቹ ላይ ተነስቶባቸዋል፤ የወያኔ ጦርም በክፍፍል እየተቦረቦረ ነው:: አገዛዙ ለውድቀት ተመቻችቷል ቢባል ተገቢ ነው:: ይህ

በመባሉ ግን በድንገት በነፋስ ይወድቃል ወይም በራሱ በቃኝ/ አቃተኝ ብሎ ስልጣን ይለቃል ማለት አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ሊወድቅ ሊወገድ የሚችለው ባመረረ ትግል ነው።

ይህ ግልፅ ሆኖ እያለ ዛሬም አጓጉል ፍቅርን እየሰበኩና በወያኔ ላይ መደገን የሚገባውን ጠመንጃ ሊቀብሩ የሚጥሩ መኖራቸውም መሳት የለበትም። ፍቅር ያሻል፣ ጥላቻ ጎጂ ነው፣ ከወያኔም ቢሆን እንወያይ፣ የአንድ ሀገር ልጆች ነን፣ ወዘተ በሚል ትጥቅ አስፈቺ ሀሳዊ መሲሆች በምሁር ና ታጋይም ሽፋን የሕዝብን ጎራ እያደነቆሩ ናቸው። ሀገሩን ሊቀማ ያለ ሕዝብ፣ መብቱን የተነጠቀ ሕዝብ፣ ከጠላቱ ጋር እንዲፋቀር ወይም እንዲተቃቀፍ መስበክ መቼም ቢሆን ለጠላት ለመጥቀም የተነሳ መሆኑ ግልፅ ነው። ጠመንጃ ይወለወላል እንጂ አይቀበርም፣ ይወደራል እንጂ በወያኔ ላይ አይዘቀዘቀም። ጠላትን መውደድ ሰበካ ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ኢትዮጵያንና ሰብዕናችንን የሚያሳጣን ይሆናልና ሊታሰብም አይገባውም። ሀገር ለቅርጫ ስትቀርብ ሽንፍላም ቢሆን ይጣል ልን ብለው የሚሰለፉ ትግልን አውግዘው ፍቅርና ዕርቅን ቢሰብኩ የሚያስገርም አይሆንም። ሆድ ሲቀድም ህሊናና ወኔ ይከሳሉ፣ይሞታሉ። ከወያኔ ጋር ተቃቅፈው ተጠቃሚ ለመሆን የተኮለኮሉት ዘረኞችና አድርባዮች ሁሉ ተኙ አትታገሉን ቢሰብኩ የሚጠበቅ ነው። ነገ ግን እነሱም እንደ ወያኔ ለሕዝብ ፍርድና ጥቃት መዳረጋቸው የማይቀር ነው። ያ ቀን ደግሞ ቀርቧልናም ዋ! ስንል በባዶ አይደለም። ጆሮ ያለውና ያልወየነ ሁሉ ይስማ!!

መለስ ዜናዊ 1997 የፈፀምነውን ስህተት አንደግምም ብሏል--ሀዝብ መፍጀቱን ሳይሆን በምርጫ መሸነፉን ማለቱ ነው። ሕዝብም የ1997ኡን አመፅ ሊደግም የሚችለው የያኔውን ስህተቱን አስወግዶ ብቻ ነው። ቆራጥ መሪዎችን ደግፎ፣ ከአስመሳይ ታጋዮች ርቆ፣ ወያኔን ጠላት ብሎ ለማስወገድ በቁርጠኛነት ተነሳስቶ፣ ወያኔ በሰላም ወይም በምርጫ ተሸነፍኩ ብሎ ስልጣን የማይለቅ መሆኑን በሚገባ ተገንዘቦ ለሀገሩና ለመብቱ የሞት ሽረት ትግልን ሊያካሂድ ሲነሳ ነው።

ፀረ ወያኔው ትግላችን ይፋፋም!!